# ምዕራፍ አምስት

# የሀገር ፍቅር

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- የሀገር ፍቅር መገለጫዎችን ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ::
- የሀገርን ታሪክ ማወቅ ለሀገር ፍቅር መጐልበት ያለውን ጠቀሜታ ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ::
- የበጐ ፈቃድ አገልግሎት ዓላማን ትረዳለህ/ትረዳለሽ::
- ዜግነት የሚገኝባቸውን መንገዶች ታውቃለህ/ታውቂያለሽ::

## 5.1 የሀገር ፍቅር፤

### 5.1.1 ለሀገር ፍቅር መጐልበት የማያስፈልጉ ሁኔታዎች፣

ባለ ብዙ ቋንቋ - ባለ ብዙ ዜማ፣
አኩሪ ታሪካችን - በዓለም የሚሰማ፤
የዕድገት ጐዳናችን - መንገዱ የሰፋ፣
የሠላም ሕዝቦች ነን - ባለ ብሩህ ተስፋ።
ባንድ እንደሚበሩ - የሠላም ርግቦች፣
ባለ ብዙ ቀለም-ህብርነን-ውብ ሕዝቦች፤
ኢትዮጵያ ልጆችሽ - ቃል እንገባለን፣
ለዕድገትሽ ልንሰራ - ላብና ደም ከፍለን።
*(ከህብረ ብሔር መጽሔት፤ህዳር 2000.ዓ.ም)*

- ከዚህ በላይ የቀረበው ግጥም ምን ምን ይዘቶች እንዳሉት ግለፁ::
- በግጥሙ ውስጥ ህብረ ብሔራዊነት የተገለፀው እንዴት ነው?

**የተማሪዎች ክርክር፤**

የአድዋ ድል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በየሦስት ወሩ የክርክር ፕሮግራም አላቸው። የዚህ ወር ተከራካሪዎች የስድስተኛ "ሀ"፣ "ለ" እና "ሐ" ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ለመከራከሪያነት የተሰጠው ርዕስም፤ "ለሀገር ፍቅር መጎልበት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች" የሚል ነው። የስድስተኛ "ሀ" ክፍልን ወክለው የሚከራከሩት ኤልሳቤጥና ዳንኤል ናቸው። እነዚህ ሁለት ተማሪዎች ለመከራከሪያነት የመረጡት ርዕስ፤ "የሀገር ፍቅርን ለማጐልበት የግልና የቡድን መብቶች መከበር አለባቸው" የሚል ነው። በዚህ ርዕስ ዙሪያ ምን ምን ነጥቦችን ቢጠቃቅሱ በክርክሩ ሊያሸንፉ እንደሚችሉ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተመካከሩ ነው።

የስድስተኛ "ለ" ክፍልን ወክለው የሚከራከሩት ሐሊማና ዘሪሁን ናቸው። እነዚህ ሁለት ተማሪዎች የሚከራከሩበት ርዕስ "የሀገር ፍቅርን ለማጐልበት አድሎአዊ አሠራር ሊወገድ ይገባል" የሚል ነው። የክፍል ጓደኞቻቸውም የሚከተሉትን ነጥቦች ለመከራከሪያነት እንዲያቀርቡ ምክር ሰጥተዋቸዋል።

ሀ. በሀገሪቱ የፍትሕ አሠጣጥ ዙሪያ አድሎአዊ አሠራር ጐልቶ ከታየ ዜጐች ለሀገራቸው የሚኖራቸው ፍቅር አናሳ ይሆናል።
ለ. በሴቶችና በወንዶች መካከል የትምህርትና የሥራ ዕድል ለማግኘት አድልዎ ከተደረገ ለሀገራችን የሚኖረን ፍቅር ይቀንሳል።
ሐ. ሰው ሁሉ በተፈጥሮው እኩል ስለሆነ ለህፃናት፣ ለአረጋዊያን ወይንም ለሴቶች የተለየ ጥበቃና እንክብካቤ ሊደረግ አይገባም።

የስድስተኛ "ሐ" ክፍልን ወክለው የሚከራከሩት አበባየሆሽና አህመድ ናቸው። አበባየሆሽና አህመድ የሚከራከሩበት ርዕስ፤ "የአካባቢንና የሀገርን ታሪክ ማወቅ ለሀገር ፍቅር ስሜት መጐልበት ያግዛል" የሚል ነው። አበባየሆሽና አህመድ የመከራከሪያቸውን ነጥብ የከፈሉት በሚከተሉት ሦስት ንዑሳን ርዕሶች ዙሪያ ነው።

1. የሀገር ፍቅር ስሜት ማደግ የሚጀምረው የቤተሰብን ታሪክ በማጥናትና በሚገባ በማወቅ ነው።
2. በአካባቢያችን ላሉ ልዩ ልዩ የታሪካዊ መገለጫዎችና ለብሔሮችና ብሔረሰቦች ባህሎች ልዩ ትኩረት ስንሰጥ የሀገር ፍቅር ስሜታችን ያብባል።
3. ለሀገራችን አኩሪ የሕዝቦች ታሪክ በቂ ዕውቀት ሲኖረን የሀገር ፍቅር ስሜታችን ፅኑ መሠረት ይኖረዋል።

**መልመጃ 1**

*በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. ኤልሳቤጥና ዳንኤል ክርክሩን ማሸነፍ እንዲችሉ በርዕሱ ዙሪያ ምን ነጥቦችን እንዲያነሱ ትመክሯችዋላችሁ?
2. ሐሊማና ዘሪሁን ጓደኞታቸው ለመከራከሪያ በሰጧቸው ከሀ-ሐ በተጠቀሱት ነጥቦች ላይ ትስማማላችሁ? ተወያዩበት፡፡
3. አበባየሆሽና አህመድ ማንሳት የሚገባቸውን ዝርዝር ነጥቦች በተመለከተ ከክፍል ጓደኞታችሁ ጋር በቡድን ተወያይታችሁ አጭር የጽሁፍ ሪፖርት ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

የሀገር ፍቅር ስሜት የሚጎለብተው የእያንዳንዱ ዜጋ የግልና የቡድን መብቱ ከአድሏዊነት በጸዳ መልኩ ሲከበርለት ነው። የብሔሮችና የብሔረሰቦች መብት ሳይሸራረፍ ሲከበር፣ የሕግ የበላይነት ሲሰፍን፣ ጠንክሮ መማርና መሥራት የዜጎች ባህል ሲሆን የሀገር ፍቅር ስሜት ከፍ ይላል፡፡

ነገር ግን የዜጎች መብት ሳይከበር የሀገሪቱን መልክዓ ምድር ማፍቀርና መውደድ ብቻ በራሱ ትርጉም አይኖረውም። አድሏዊ አሠራር በሰፈነበት ማሕብረሰብ ውስጥ የሀገር ፍቅር ስሜት ከመጎልበት ይልቅ የደበዘዘ ይሆናል። ሀገርን ከማንኛውም አደጋ መከላከልና ራስንም ሆነ ሀገርን ከሚጐዱ ጉዳዮች መጠበቅ ሀገሩን የሚወድ ዜጋ መገለጫ ነው፡፡

**መልመጃ 2**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

1. መልክዓ ምድርን ማድነቅ ብቻ በዋነኛነት የሀገር ፍቅር መገለጫ ሲሆን አይችልም የሚባለው ለምንድን ነው?
2. አድሏዊነት የሚይታይበት የሕዝቦች መፈቃቀርና መከባበር ውጤቱ ምን ሲሆን ይችላል?
3. እናንተስ ሀገራችሁን መውደዳችሁን የምትገልፁት ምን በማድረግ ነው?

## 5.2 ጉዲና አፍራሽ ተግባራት፤

### 5.2.1 ለጋራ ንብረቶች እንክብካቤ አለማድረግ፣

- የጋራ መገልገያ ንብረቶች የሚባሉት ምንድን ናቸው?

**አርአያነት ያለው ተግባር፤**

የዕውቀት ፋና ትምህርት ቤት፤ "የሀገር ፍቅር" በሚል ስያሜ የሚታወቅ ክበብ አለው። የትምህርት ቤቱ "የሀገር ፍቅር ክበብ" አባላት መምህራንና ተማሪዎች ናቸው። የክበቡ አባላት በየጊዜው በሚያደርጉት አርአያነት ያለው እንቅስቃሴ ዩኒሴፍ (የተባበሩት መንግሥታት የህፃናት መርጃ ድርጅት) ከሚባል ዓለም አቀፍ ድርጅት ልዩ ሽልማት ሊያገኙ ችለዋል። በቅርቡ በትምህርት ቤታቸው ግቢ ውስጥ ያዘጋጁት ልዩ ዐውደ ርዕይ ብዙ ተመልካቾችን አስደንቋል። ዝግጅቱ የቀረበው በዓመታዊ የትምህርት ቤቱ በዓል ላይ ስለነበር በርካታ ወላጆች ተገኝተው ነበር። ዝግጅቱ የቀረበው በሦስት ክፍሎች ተከፋፍሎ ሲሆን የዝግጅቱ ይዘትም የሚከተለውን ይመስላል። የመጀመሪያው ክፍል ትርዒት የቀረበው በትምህርት ቤቱ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ነው። የቤተ መጻሕፍቱን ዋና በር ሲገቡ የተቀዳደዱና ስዕሎቻቸው ከውስጥ ተቦጭቆ የተወሰዱ በርካታ መጻሕፍት ይታያሉ። በግርግዳውም ላይ "ትውልድ ይፍረደን" የሚል ጽሑፍ ተጽፏል።



ሥዕል 5.1 የተገነጣጠሉና የተቀዳደዱ መፃሕፍት

በሁለተኛው ክፍል ውስጥ በግዴለሽነት የተሰ ባበሩ ወንበሮች፣ ጥቁር ሰሌዳዎች፣ ዴስኮችና የቤተ ሙከራ ዕቃዎች ተሰብስበዋል፤ በግድግ ዳውም ላይ "በግዴለሽነት የተጐዱና የተሰባ በሩ የጋራ መገልገያዎቻችን" የሚል ጽሑፍ ይነበባል።



ሥዕል 5.2 በግዴለሽነት የተጐዱና የተሰባበሩ የጋራ መገልገያዎቻችን

በሦስተኛው የትርዒት ማሳያ ክፍል ተማሪ ዎች በጫጭቀው የጣሏቸው ደብተሮች፣ የገነ ፈሉ እስክሪቢቶዎችና ቁርጥራጭ እርሳሶች ተሰብስበው ይታያሉ። በግርግዳውም ላይ "ከዚህ ውስጥ ያንተ/ቺ የትኛው ነው?" የሚል ጽሁፍ ተጽፏል።




ሥዕል 5.3 የገነፈሉና የተሰባበሩ እስክሪፕቶዎችና እርሳሶች

ዝግጅቶቹ ተጠናቀው ጎብኚ እንግዶቹ ከየክ ፍሎቹ ሲወጡ በራፍ ላይ በቆሙ አስተናጋጅ ተማሪዎች አማካይነት አነስተኛ ካርድ ታደ ላቸው፡፡ በካርዶቹ ላይ የተጻፈው ጽሑፍ እንዲህ የሚል ነው። "እኛስ አንዴ በግዴለ ሽነት ተፈርዶብናል፤ ለቀሪዎቹ መጻሕፍትና የመማሪያ መሣሪያዎች እንክብካቤ እንዲ ደረግላቸው አደራችንን እስተላልፉልን።"

**መልመጃ 3**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. ከላይ የቀረበው «የሀገር ፍቅር ክበብ» አባላት ምሳሌያዊ ትርዒት ምን ስሜት አሳደረባችሁ?
2. እናንተስ የትምህርት ቤታችሁን የጋራ መገልገ ያዎች እንዴት ነው የምትይዙት?

በትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ለመማር ማስተማሩ ሂደት በጣም ወሳኝ ናቸው። ሀገራችን ካላት ውስን ሃብት ተቆንጥሮ ለትምህርት ቤቶች የጋራ መገልገያ እንዲሆኑ የሚሟሉት መሣሪያዎች በጥንቃቄ መያዝ ይገባቸዋል። የመማሪያ ወንበሮች ከጥን ቃቄ ጉድለት የተነሣ ቢሠበሩ ጉዳቱ የተማ ሪው ነው። የክፍል ወለሉ ቢቆፋፈር የጤና ጉዳት የሚያስከትለው በራሱ በተማሪውና በመምህሩ ላይ ነው። የጋራና የግል መገልገያ

*መሣሪያዎች ጥንቃቄ በጎደለበት ሁኔታ መያዝ ጉዳቱ ከራስ አልፎ የሚጎዳው ቤተሰብንና ሀገርን ስለሆነ እያንዳንዱ ዜጋ ሃላፊነት አለበት።*

## ✎ የቡድን ሥራ 3

*ጉዳት እንዳይደርስባቸው ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚገቡ የትምህርት ቤታችሁን የጋራ መገልገያ ንብረቶችን በመዘርዘር እንዴት ሊጠበቁ እንደሚገባቸው በቡድን ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ የጽሁፍ ሪፖርት አቅርቡ።*

### 5.2.2 ቆሻሻን በየቦታው መጣል፣ በመፀዳጃ ቤት በአግባቡ ያለመጠቀምና ግዴለሽነት፣

- ቆሻሻን በየቦታው መጣልና በመፀዳጃ ቤት ባግባቡ ያለመጠቀም ምን ጉዳይ ሊያስከትል ይችላል?

**የንፁህ መንደር ክንውኖች፤**

የንፁህ መንደር ወጣቶች በፈቃደኝነት ተሰብስበው የስካውት ቡድን አቋቁመዋል። የስካውት ቡድኑ አሥራ ሁለት አባላት ያሉት ሲሆን ዋነኛ ሥራቸውም የአካባቢያቸውን ጽዳት ማስጠበቅ ነው። ለወጣቶቹ ሙሉ የደንብ ልብስ አዘጋጅቶ የሰጣቸው የቀበሌአቸው ጽ/ቤት ነው። ወጣቶቹ ራሳቸውን በተራ ደልድለው በመኖሪያ ሰፈራቸው አካባቢ እየተዟዟሩ አካባቢያቸውን ያፀዳሉ፣ የጽዳቱንም ሁኔታ ይከታተላሉ፡፡ የውሃ መውረጃ ቦይ እንዳይደፈን፣ የሰፈሩ ወጣቶች የመጫወቻ ሜዳ እንዳይቆሸሽ በጥብቅ ይቆጣጠራሉ።

ነዋሪው ኅብረተሰብ ቆሻሻ በየቦታው እንዳይጥል ትምህርት ይሰጣሉ፣ ልዩ ልዩ ጽሑፎችንና ፖስተሮችንም በመለጠፍ ይቀሰቅሳሉ። እነርሱም ምሳሌ በመሆን ሠርተው ያሠራሉ፡፡ በአካባቢያቸው ከለጠፏቸው ጽሑፎች መካከልም፤

"ቆሻሻ የሚያቆሽሸው ራስን ነው!"
"እኔና ቆሻሻ አንገናኝም!"
"ሰፈሬ በፅዱነቷ ይታወቅ!"
"መፀዳጃ ቤቴ ንፁህ ነው"
"ግዴለሽነት በሰፈሬ አይታወቅም!" የሚሉት ይገኙበታል።

ስካውቶቹ ባሉበት ሰፈር ቆሻሻ የሚደፉ ወይንም በየመንገዱ የሚያዝረከርኩ ሰዎች አይታዩም፡፡ የጋራ መፀዳጃ ቤቶቹን ንፅህና የማይጠብቅና በግዴለሽነት ለአካባቢው ነዋሪዎች ጤንነት ጎጂ የሆነ ተግባር ሲፈፅም የተገኘ ሰው አካባቢው በመረጣቸው ዳኞች ቅጣት ይወሰንበታል።

የስካውት አባላቱን ሥራ የሚተችና ሥራው እንዳይሠራ እንቅፋት የሚሆን ማንኛውም ሰው በተመረጡት ዳኞች ቅጣትና ግሣፄ ይደርስበታል፡፡ በዚህም ምክንያት የቆሻሻ መጣያ የነበሩ ሥፍራዎች የጓሮ አትክልት ማልሚያ ሆነዋል። የቆሻሻ መጣያ ገንዳዎችና የመፀዳጃ ቤቶቹም በንፅህና ሊጠበቁ ችለዋል። ይህን በመሰለው አርአያነት ያለው የወጣቶቹ ተግባርም መንደሩ "ንፁህ" የሚል ስያሜ አግኝቷል።

**መልመጃ 4**

*በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. የንፁህ መንደር ስካውቶች ተግባር ምን ትምህርት እንደሰጣችሁ ስንደኞቻችሁ አካፍሏቸው፡፡
2. የአካባቢያችሁ የፅዳት ሁኔታ ምን ይመስላል?
3. እንደ ንፁህ መንደር ስካውቶች በእናንተስ አካባቢ ምሳሌ የሆኑ ወጣቶች አሉ?



ሥዕል 5.4 ቆሻሻ ባግባቡ ካልተወገደ ለጤና ጠንቅ ይፈጥራል፡፡



ሥዕል 5.5 የጋራ መጸዳጃ ቤቶች ንጽሕናቸው የተጠበቀ መሆን አለበት

- ከሥዕሎቹ ምን ትማራላችሁ?
- በእናንተ አካባቢስ እንዲህ ዓይነት ችግር አለ?

ቆሻሻን በየቦታው መጣልና ማዝረክረክ በጤና ላይ ከፍተኛ ቀውስ ያስከትላል፡፡ የቆሻሻ መጣያ አካባቢዎች በጽዳት ካልተያዙ ከቆሻሻው ላይ የሚነሱት ዝንቦች በአካባቢው ነዋሪ ላይ የጤና ችግር ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ያልተከተቡ ውሾች፣ ጅብና የመሳሰሉት አውሬዎችም በዚያ አካባቢ ስለሚርመሰመሱ ከፍ ያለ ጉዳት ሊከተል ይችላል። የመጸዳጃ ቤትን በጥንቃቄ ካለመያዝ የተነሳም በተላላፊ በሽታዎች ምክንያት የአካባቢው ነዋሪ ሊጎዳ ይችላል። እነዚህን መሰል ግዴለሽ ተግባራት እንዲታረሙም የአካባቢው ወጣቶች ከፍተኛ ተግባራትን ሊያከናውኑ ይችላሉ።

**መልመጃ 5**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

1. በአካባቢ መቆሸሽና የመፀዳጃ ቤትን በንፅህና ካለመያዝ የተነሳ ሊከሰቱ ስለሚችሉ ችግሮች በቡድን ተወያዩባቸው፡፡
2. በአካባቢያችሁ ግዴለሽነት የሚስተዋልባቸውን ጉዳዮች እያነሳችሁ በቡድን ተወያዩባቸው፡፡
3. «አካባቢዬን በንፅህና ስመጠበቅ የእኔ ድርሻ» በሚል ርዕስ አጭር ጽሑፍ በቡድን ፅፋችሁ አቅርቡ፡፡

## 5.3 በጐ ባህርያት፤

### 5.3.1 ማንኛውም አፍራሽ ተግባር መቃወም፣

"ጽድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም፣
ከክፉት ደግነት ሳይሻል አይቀርም።"
*(ሕዝባዊ ግጥም)*

- ይህ ሕዝባዊ ግጥም በጐ ባህርያትን እንድናዳብር ምን ትምህርት ይሰጣል?

**ታማኙ ውሻ፤**

አንድ አርሶ አደር በጣም የሚወደው ታማኝና በባህርይው የተመሰገነ ውሻ ነበረው። ይህ ውሻ የጌታውን ቤት ተግቶ ይጠብቅ ነበር። ሌሎች አራዊቶችም ግቢውንና ከብቶቹን እንዳይደፍሩ በንቃት ይከላከል ነበር። በዚሁ ውሻ ምክንያት የዚህን አርሶ አደር ቤት ሌቦች ሊደፍሩ አልቻሉም። ይህ ገበሬ በአንድ ወቅት ገንዘብ ቢቸግረው ለአንድ ባለጠጋ ሰው ውሻውን አሲዞ ገንዘብ ተበደረ። ብድሩን ከፍሎ እስኪያጠናቅቅም ውሻውን ለአበዳሪው አሳልፎ ሰጠው።

ያ ውሻ የጌታውን ችግር ተረድቶ የአበዳሪውን ቤትና ንብረት ልክ እንደ ቀድሞ አሳዳሪው ቤት በትጋት እየጠበቀና ከሌቦች እየተከላከለለት በታማኝነት ያገለግለው ጀመር። አንድ ቀን የአበዳሪው ልጅ በአልጋው ላይ ተኝቶ ሳለ አንድ ትልቅ እባብ በጣራው ላይ እየተምዘገዘገ መጣ። ውሻው የዚያን እባብ እንቅስቃሴ ይከታተል ኖሮ በፍጥነት ዘሎ እባቡን ቦጫጭቆ በመግደል ልጁን አዳነ።

የዚህን ውሻ መልካም ተግባር የተገነዘበው ሁለተኛው አሳዳሪ በውሻው ድርጊት ተደስቶ ወደ ቀድሞው ጌታው አመስግኖ ሊመልሰው ወሰነ። በአንገቱ ላይ የምሥጋና ቃል ጽፎ በማሰርም ውሻውን መርቆ ሰደደው። ነገር ግን ውሻው በሌብነቱ ያጋለጠውና የውሻውን ባለቤት የማይወድ አንድ ሰው ውሻውንና ጌታውን ለማጣላት ተንኮል በመጠንሰስ በውሻው ላይ ጉዳት እንዲደርስ አንድ ዘዴ ፈጠረ።

ወደ ጌታው ቤት ቀድሞ በመሄድም ውሻው ለሁለተኛው ጌታው እንደማይታዘዝና ጌታውም በጣም ስለተቸገረ ወደ እርሱ ሊመልሰው እንደሚያስብ ተንኮሉን አቀነባብሮ ነገረው። የውሻው ጌታም በውሻው ድርጊት በጣም አዝኖ የተበደረውን ገንዘብ ለመመለስ ወደ አበዳሪው ቤት እየገሠገሠ ሳለ ውሻው ወደ እርሱ እየሮጠ ሲመጣ መንገድ ላይ ተገናኙ። ውሻው ጌታውን እንዳየ በደስታ እየሮጠ በመቅረብ ፍቅሩን እንደወትሮው ይገልፅለት ጀመር። ነገር ግን ጌታው በሰማው የተንኮል ወሬ ተበሳጭቶ ውሻው ከአበዳሪው ቤት አምልጦ የመጣ ስለመሰለው በያዘው ዱላ አንዴ ቢያሳርፍበት ውሻው ወዲያው ሞተ።

ገበሬው የውሻውን ሬሣ ቆሞ በሀዘን ሲያስተውል በአንገቱ ላይ የታሰረ ወረቀት አገኘ። ወረቀቱን ገልጦ ሲያነብም የውሻውን በጎ ተግባር የሚዘረዝር የምሥጋና ቃላት የተጻፈበት ደብዳቤ መሆኑን ተረዳ። ስለ ውሻው መልካም ባህሪም ባለፀጋው ሰው የገበሬውን ዕዳ እንደ ማረው ይገልጻል። የውሻው ጌታ ምሥጢሩን ሲረዳ ስቅሰቅ እያለ በማልቀስ በሥራው ተጸጸተ።

*(ከበደ ሚካኤል፣ ተረትና ምሣሌ፣ 2ኛ መጽሐፍ፣ 6ኛ ዕትም 1994ዓ.ም ሊዚህ ክፍል እንዲመጥን ተደርጎ የተወሰደ)*

**መልመጃ ፍ**

*ከላይ የቀረበውን ታሪክ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

?

1. የውሻው መልካም ተግባር የተገለጠው እንዴት ነው?
2. ያለ አድልዎ የጌታውንና የአሳዳሪውን ቤት በእኩልነት ስላገለገለው ውሻ መልካም ተግባር ምን ትምህርት አገኛችሁ?
3. ውሻው ሊሞት የቻለው ለምን ነበር?
4. ውሻ እዲህ ሌባን በማጋለጥና መልካም ተግባር የሚያሳይ ከሆነ ከእናንተስ ምን ምን ዓይነት መልካም ተግባርና ባህርያት ይጠበቃሉ?

በጎ ባህርያት የመልካም ሰብዕና ማጣፈጫ ቅመሞች ናቸው። በጎ ባህርያት በቅድሚያ የሚጠቅሙት ራስን ነው። በበጎ ባህርይው የሚመሰገን ሰው ሁልጊዜም የህሊና እርካታ ይጎናፀፋል።

የታመመ ሰውን መጠየቅ፣ የተቸገረን መርዳት፣ ተስፋ የቆረጠን ሰው ማፅናናት፣ ለታላላቆችም ሆነ ለታናናሾች ተገቢውን አክብሮት መስጠት በውዴታ ብቻ የምናደርገው ሳይሆን ሰብአዊ ግዴታችንም ጭምር ነው። ለራሳችን የህሊና እርካታ ብለን የምናሳያቸው በጎ ባህርያት ለሌሎችም ሊጠቅሙ ይችላሉ፡፡

በጎ ባህርያት ለቤተሰባችን አባላት፣ ለጎረቤቶቻችን፣ ለአካባቢያችን፣ ለትምህርት ቤት ጓደኞቻችንና ለጠቅላላው ማኅበረሰብ ማሳየት የአስተዋይ ሰው መለያ ባህርያት ናቸው። በጎ ባህሪያት የሌላቸው ሰዎች በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚኖራቸው ተቀባይነት እጅግ አናሳ ይሆናል።

ሌሎችን ሊጎዱ የሚችሉ አፍራሽ ተግባራትንና አድሎአዊ አሠራርን በፅናት መቃወምም የበጎ ባህርይ ሌላው ገጽታ ነው።

ለምሳሌ በሌብነት ላይ የተሰማራ ሰው በአካባቢያችን መኖሩን እያወቅን በቸልታና በይሉኝታ ብናልፍ እኛም የጥፋቱ ተባባሪዎች መሆናችንን መረዳት ይገባናል።

አንድ ሰው በሌባ ሲጠቃ እያየን እንዳላየ ሆነን ብናልፍ እኛንም ነገ ተመሳሳይ ችግር ቢገጥመን የሌላውን ሰው ትብብር ለመጠየቅ እንዴት እንችላለን?

**መልመጃ 7**


*የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ በመገልበጥ ልታዳብሯቸው የሚገቡ በጐ ባህሪያት ንና ልታስወግዳቸው የሚገቡ አፍራሽ ተግባራትን እየለያችሁ አመልክቱ፡፡*

| ልናዳብራቸው የሚገቡ በጐ ባህርያት (ተግባራት) | ልናስወግዳቸው የሚገቡ አፍራሽ ተግባራት (ባህሪያት) |
|---|---|
| በቤት ውስጥ፤<br>ምሳሌ፤<br>1.ለታላላቆች መታዘዝ።<br>2.<br>3.<br>በትምህርት ቤት ውስጥ፤<br>ምሳሌ፤<br>1. ሰዓትን አክብሮ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት።<br>2.<br>3.<br>በአካባቢዬ፤<br>ምሳሌ፤<br>1. አርዓያነት ያለው ተግባር መፈጸም<br>2.<br>3. | በትምህርት ቤት ውስጥ<br>ምሳሌ፤<br>1. የጋራ መገልገያ የሆኑ ንብረቶችን የሚያበላሹትን ተማሪዎች ፊት ለፊት አለማጋለጥ።<br>2.<br>3.<br>በአካባቢዬ፤<br>ምሳሌ፤<br>1. ለአካባቢ ንጽህና ችግር የሚፈጥሩትን በግልጽ አለመቃወም።<br>2.<br>3.<br>በቤት ውስጥ<br>ምሳሌ፤<br>1. በውሸት የቤተሰብ አባላትን ማጋጨት<br>2.<br>3. |

## 5.4 ድህነትን ማስወገድ፤

### 5.4.1 ድህነትን ለማስወገድ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አስፈላጊነት፣





ሥዕል 5.6 ተግቶ በመሥራት ድህነትን ማስወገድ ይቻላል፡፡

- *አንዱን ሥዕል ከሌላው ጋር በማነፃፀር ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፉ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት?*

### የእፎይታ ሰፈር ልጆች፤

ዳምጤ፣ ቦንገር፣ ረዳኢና ሳጉሬን ያስተዋወቃቸው መጥፎ አመላቸው ነበር። ሁሉም ወጣቶች፣ ይሠርቃሉ፣ ይሰክራሉ፣ ለተለያዩ ሱስ አስያዥ ዕፆችም ተገዢዎች ነበሩ።በዚህም ያልተገባ ባህርያቸው ምክንያት ቤተሰቦቻቸውና የአካባቢያቸው ሰዎች እጅግ ተማረው ነበር። በየጊዜው በፖሊስ እየተያዙ ስለሚታሠሩም ከሰፈር በጠፉ ጊዜ ሁሉ እነዳምጤ የት ሄዱ ሲባል፤ "ካምቦሎጆ ገብተዋል" ይባል ነበር።

ካንቦሎጆ የሚሉት እስር ቤትን ነው። በዚህ ዓይነት ሕይወት የእድሜያቸውን ግማሽ ከኖሩ በኋላ በአንድ ወቅት ቢርቢርሶ በሚባል በአካባቢው አርአያነት በነበረው ወጣት አማካይነት ሕይወታቸው ተለወጠ። ቢርቢርሶ ባደረገው ያላሰለሰ ምክርም አራቱም ወጣቶች ከተለያዩ ሱሶቻቸው ሙሉ ለሙሉ ተላቀቁ። መንግሥት በተለይ ለወጣቶች በነደፈው የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑም በቀበሌአቸው ጽ/ቤት አማካይነት የመኪና እጥበት ሥራ እንዲጀምሩ ሁኔታዎች ተመቻቹላቸው።

ዳምጤ፣ ቦንገር፣ ረዳኢና ሳጉሬ የመኪና እጥበት ሥራቸውን በከፍተኛ ታማኝነትና ትጋት ስለሚያከናውኑ በደንበኞቻቸው ዘንድ መወደድና ዝና የተጐናፀፉት በአጭር ጊዜ ነው። በሥራቸውም ስኬታማ ስለሆኑ በርካታ ሃብት ለማከማቸት ችለዋል። አካባቢውን ያስቸግሩ ሌሎች ጓደኞቻቸውንም ሥራ እየሰጧቸው ሕይወታቸውን መለወጥ ችለዋል።

አልፎ ተርፎም አስር ልጆችን ከጐዳና ሕይወት በማውጣት ለልብሳቸው፣ ለምግባቸውና ለትምህርታቸው ተገቢውን በጀት በመመደብ እያስተማሯቸው ይገኛሉ። እነዚህ አራት ጓደኞሞች በአቋቋሙት ድርጅት ስም መነሻነትም ቀደም ሲል አካባቢው የሚታወቅበት ስም ተለውጦ "እፎይታ" የሚል ስያሜ ተሰጠው።

*(በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በ1999 ዓ.ም ተደጋግሞ ከቀረበ የወጣቶች ታሪክ ተሻሽሎ የተወሰደ)*

**መልመጃ ፰**

***ከላይ የቀረበውን ታሪክ መነሻ በማድረግ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***

1. ከዳምጤና ጓደኞቹ የሕይወት ለውጥ በኋላ የሕይወት ለውጥ ምን በጐ ውጤቶች ተገኘ?
2. ቀደም ሲል ወጣቶቹ በነበራቸው ዓይነት የተበላሸ ሕይወት ለመለወጥ ምን መደረግ አለበት?
3. ድህነትን ከሀገራችን ለማጥፋት የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ያላቸው ጠቀሜታ ምን ሊሆን እንደሚችል በበድን ተወያዩበት።

ሀገራችን የበርካታ የተፈጥሮ ሀብትና የታሪካዊ ቅርሶች ባለቤት ነች። እነዚህን መሰል ታሪካዊና ተፈጥሯዊ መኩሪያዎች ቢኖሩንም በአንጻሩ ግን ብዙ ችግሮች አሉብን።

የተፈጥሮ ሀብት ቢኖረንም ለሥራ የተነቃቃና ለአዳዲስ ፈጠራ የተነሣሣ በቂ የሥራ ኃይል መፍጠር ስላልተቻለ ሀገራችን በዓለም ፊት በድህነት ለመታወቅ በቅታለች። አስከፊው የድህነታችን ገጽታም በልዩ ልዩ አቅጣጫ ሀገሪቱንና ዜጐቿን ሲያሸማቅቅ ኖሯል። ይህንን ለዘመናት ተከትሎን የመጣውን ድህነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ታግሎ ለማሸነፍ መንግሥት በርካታ ውጤታማ የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ዘርግቷል።

ለልማት ፖሊሲዎቹና ስትራቴጂዎቹ ተፈፃሚነትና ውጤታማነት እያንዳንዱ ዜጋ ተግቶ በመማርና በመሥራት ሀገሩን የማበልፀግ ኃላፊነት አለበት። መደበኛ ኃላፊነትን መወጣት ብቻ ሳይሆን ለበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት ራስን ማሳተፍም ድህነትን ለመቅረፍ አንዱ ዘዴ ነው።

"የመንግሥት ጉዳይ ነው" ከማለት ይልቅ ጉዳዩ ይመለከተኛል ብሎ የድርሻን መወጣት የመነግሥትን የልማት ፖሊሲዎቹንና ስታራቴጂዎቹን ውጤታማነት ይበልጥ ያጐለብታል።

**መልመጃ ፱**

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ።***

1. በቤተሰብ፣ በአካባቢና በሀገር ደረጃ የድህነት መገለጫ ሊሆኑ በሚችሉ ነገሮች ላይ በቡድን ተወያዩ።





ሥዕል 5.7 የበጐ ተግባር የዜጎች የውዴታ ግዴታ ነው

- ሥዕሎቹ ምን መልዕክት ያስተላልፋሉ?

በቤት፣ በአካባቢና በትምህርት ቤት ውስጥ የእኛን በጐ ፈቃደኝነት የሚጠይቁ በርካታ ተግባራት አሉ። በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ ጥቂቱን ለማመልከት ተሞክሯል።

| በቤት ውስጥ | በአካባቢ | በትምህርት ቤት ውስጥ |
|---|---|---|
| 1. የወላጆችን ትዕዛዝ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን አስቀድሞ ዕቅድ በመንደፍ የግልና የጋራ ኃላፊነትን መወጣት:: 2. የመኖሪያ ቤትንና ግቢን በንፅህና መጠበቅና በራስ ፈቃድ ውበትን መፍጠር:: | 1. ረዳት የሌላቸውን፣ አቅመ ደካሞችንና አረጋዊያንን መንከባከብ:: 2. ከሠፈር ጓደኞች ጋር በመሆን የአካባቢን ፅዳት መጠበቅ:: 3. ለጐረቤትና ለዘመድ አቅም የፈቀደውን ግልጋሎት መስጠት:: | 1. የትምህርት ቤታችን የስነዜጋ እና ስነምግባር ክበብ አባል በመሆን ማገልገል:: 2. የትምህርት ቤታችን ግቢ ጽዳትና ውበት እንዲጠበቅ መንከባከብ:: 3. ወደ አልተገባ ባህርይ እየሄዱ ያሉትን ተማሪዎች በመምከር የባህርይ ለውጥ እንዲያመጡ መርዳት:: |

**መልመጃ 10**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

?

1. በበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት በአካባቢያችሁና በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ብትሳተፉ ያስደስቱናል የምትሏቸውን ተግባራት ዘርዝሩ::
2. ስለሰው ልጆች የበጐ ፈቃድ አገልግሎት በመስጠት በታሪክ ውስጥ ተጠቃሽ ከሆኑ ሰዎች መካከል ስለ አንዱ ከሰዎች ጠይቃችሁ ወይንም ከመጻሕፍት አንብባችሁ ለጓደኞቻችሁ ታሪኩን አካፍሏቸው::

## 5.5 ዜግነት፤

### 5.5.1 ዜግነት የሚገኝባቸው መንገዶች፣

- ዜግነት ማለት ምን ማለት ነው? ቀደም ሲል የተማራችሁትን ትምህርት በማስታወስ ስለ ዜግነት የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው::

ዜግነት በመወለድ ወይንም በሕግ የሚገኝ መብት ተብሎ በሁለት ይከፈላል። አንድ ሰው ከወላጆቹ አንዱ ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት ከሆኑ ከኢትዮጵያዊ ዜጋ በመወለዱ ብቻ የዜግነት መብት ጥቅም ያገኛል። ኢትዮጵያዊ ወላጁ/ወላጇ በውጭ ሀገር ቢኖር/ብትኖር እንኳ የዜግነት መብቶቹን ከማግኘት የሚከለክለው ነገር የለም።

ዜግነት የሚገኝበት ሁለተኛው መንገድ በሕግ የሚገኝ ዜግነት በመባል ይታወቃል። አንድ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ሰው በራሱ ፈቃድ የኢትዮጵያዊነት ዜግነት እንዲሰጠው ለመንግሥት ጥያቄ ሲያቀርብና የሀገሪቱ ሕግ የሚጠይቀውን ሁኔታ መሟላቱ ሲረጋገጥ የኢትዮጵያዊ ዜግነት መብት ሊያገኝ ይችላል።

**መልመጃ 11**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

1. በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ስንት ዓይነት የዜግነት ማግኛ መንገዶች አሉ?
2. በመወለድ የሚገኘው የዜግነት መብት በሕግ ከሚገኘው የዜግነት መብት በምን ይለያል?
3. ከኢትዮጵያዊያን ወላጆች የተገኘ አንድ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ እየኖረ ኢትዮጵያዊ ዜግነት አልፈልግም ማለት ይችላል?

## 5.6 ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ፣

### 5.6.1 የሰንደቅ ዓላማና የብሔራዊ ዓርማ ትርጉም፣



ሥዕል 5.8 የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ

- በሰንደቅ ዓላማችን ላይ ያለው ብሔራዊ ዓርማ ምን መልዕክት ያስተላልፋል?

**ይህች ሰንደቅ ዓላማ፣**

የአብሮ መኖር ሲሳይ የድል ብሥራት ዜና፣
የሀገራችን ኩራት የሕዝቦች ልዕልና፣
ሰንደቅ ዓላማችን ሕያው ባለ ዝና፣
ዘለዓለም አዲስ ናት አታውቅም እርጅና።
ተስፋ ለምለሚቱ አበባና ፍሬ፣
ፍቅር መሥዋዕትነት የውበት ዝማሬ።
ማነው የማያለቅስ ከደስታ ብዛት፣
ማነው የማይኩራ በሀገሩ ነፃነት?
ሰንደቅ ዓላማችን ስታገኝ ከፍታ፣
ማን ይቆጣጠራል የልቡን ትርታ?
*(ታደለ ገድሌ ፀጋዬ፣ ትንቅንቅ፣ 1993 ዓ.ም)*

**መልመጃ 12**

*ግጥሙን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. ግጥሙ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ምንድን ነው?
2. በግጥሙ ውስጥ የሰንደቅ ዓላማችን ቀለም ትርጉም የተገለፀው እንዴት ነው?
3. ሰንደቅ ዓላማችን በድል የሚውለበለብበት ወቅት የተመልካቹ ስሜት ምን እንደሚመስል የተገለፀው እንዴት ነው?

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ከላይ አረንጓዴ ከመሐል ብጫ፣ ከታች ቀይ ሆኖ በመሐሉ ብሔራዊ ዓርማ እንደሚኖረው በሕገመንግሥታችን አንቀፅ3 ላይ በዝርዝር ተቀምጧል። ሦስቱም ቀለማት እኩል ሆነው በአግድም ይቀመጣሉ። የሰንደቅ ዓላማችን ሦስቱ ቀለማት የራሳቸው ትርጉም አላቸው። አረንጓዴው የሚወክለው ልምላሜንና ብልፅግናን ሲሆን፣ ብጫው ተስፋንና ብሩህ ዘመንን ያመለክታል። ቀዩ ደግሞ ጀግንነትንና መስዋዕትነትን ይወክላል።

ከሰንደቅ ዓላማው መሃል ለመሃል በሰማያዊ መደብ ላይ የተቀመጠው ብሔራዊ ዓርማ እኩል መጠን ባላቸው መስመሮች የተሳለ የኮከብ ቅርፅ ነው። ከኮከቡ የሚፈነጥቁ ነፀብራቆችም በጉልህ ይታያሉ። ኮከቡ የተሳለው በወርቃማ ቀለም ሲሆን የሚወክለው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም ሃይማኖቶች በእኩልነትና በአንድነት ለመኖር ያላቸውን ፅኑ ተስፋ ነው።

**መልመጃ 13**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. የኢትዮጵያን ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና ዓርማ ሙሉ ቀለማት ዘርዝሩ።
2. የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማችን ቀለማትን ትርጉም አንድ በአንድ አብራሩ።
3. ብሔራዊ ዓርማችን የያዘውን ትርጉም በአጭሩ ገለፁ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የግልና የቡድን መብቶች መከበር፣ አድሎአዊ አሠራር እንዳይኖር የግልን አስተዋጽኦ ማበርከት፤ የአካባቢንና የሀገርን ታሪክ ጠንቅቆ ማወቅ ለሀገር ፍቅር መጐልበት በእጅጉ ይረዳል፡፡ ጉጂና አፍራሽ ተግባራትን በመዋጋትም የሀገር ፍቅርን ማዳበር ይቻላል። በተለይም ለጋራ መገልገያ ንብረቶች ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ ከእያንዳንዱ ዜጋ ይጠበቃል። ከሰብዓዊ መገለጫችን አንዱ በጐ ባህርያትን በማሳየት ምሣሌነት ያለው ተግባር ማከናወን ነው። ነገሮችን በምንችገረኝነትና አያገባኝም በማለት ብናልፋቸው ዞሮ ዞሮ ጉዳቱ በእኛም ላይ ሊንፀባረቅ ይችላል።

ሀገራችን ከምትገኝበት የድህነት አዘቅት ውስጥ ለመውጣት እያንዳንዱ ዜጋ ማበርከት የሚገባው አስተዋጽኦ አለ። መንግሥት ለነደፋቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተፈጻሚነት ዜጐች ሁሉ የአቅማቸውን ማበርከት ይጠበቅባቸዋል። ከቤት፣ ከአካባቢና ከትምህርት ቤት ጀምረን ኅብረተሰቡን በበጐ ፈቃደኝነት ማገልገል የሰብዓዊነታችንና የዜግነታችን ግዴታ ነው።

በመወለድም ሆነ በሕግ የሚገኝ ዜግነት የሚጠይቃቸውን ግዴታዎች በአግባቡ በመፈፀም ተገቢውንም የግልና የቡድን ግዴታ መወጣት የእያንዳንዱ ዜጋ ግዴታም ኃላፊነትም ነው። ከዜግነት ኃላፊነቶች አንዱ ለብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና ለብሔራዊ መዝሙር ተገቢውን ክብር መስጠት ስለሆነ ሁሉም ዜጋ ይህንኑ መፈጸም ይጠበቅበታል፡፡

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

*መልክዓምድር፣* የመሬት ተፈጥሮአዊ ገጽታዎች።

*አድልዎ፣* ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ሌላውን ሰው ለመጥቀም የሚፈፀም ተግባር።

*የታሪክ መገለጫዎች፣* የአንድን ሀገር ሕዝብ ታሪክና ባህል የሚገልፁ ቋሚ መረጃዎች።

*ሙስና፣* ሌላውን ሰው ወይንም ራስን ለመጥቀም የሚፈፀም ሕገ ወጥ ተግባር።

*ሕዝባዊ ግጥም፣* ከትውልድ ትውልድ በቅብብሎሽ የመጡ ደራሲያቸው የማይታወቁ ግጥሞች።

*ፖሊሲና ስትራቴጂ፣* ለአንድ ተግባር አፈፃፀም መንግሥት የሚያወጣው ሕግ፣ ደንብና መመሪያ

*ዕሴት፣* አንድ ማሕበረሰብ በጠቃሚነቱ የያዘው በጐ ልማድ ወይንም ባህል።

*ስካውት፣* በበጐ ፈቃድ አካባቢውንና ነዋሪውን በነፃ የሚያገለግሉ ወጣቶች ቡድን።

*ዐውደ ርዕይ (ኤግዚቢሽን)፣* በደፋ ለሕዝብ ዕይታ የሚቀርቡ ማናቸውም ታሪካዊ ቅርሶች፣ የንግድ ሸቀጦች ወይም የምርምርና የፈጠራ አዳዲስ ግኝቶች።

*ስኬታማ፣* በተግባሩ ወይም በሥራው ውጤታማ የሆነ።

*ስብዕና፣* የሰውን ልጅ ከሌላው ፍጡር የሚለየው ተፈጥሮአዊ ባህርይ።

© MoE, FDR Ethiopia
Not to be republished

## የምዕራፍ የክለሳ ጥያቄዎች

***ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ፡፡***

***I የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆነ «ሀሰት» በማለት መልሱ፡፡***

1. ጉታችና ጊዜ ያስፈባቸው ልምዶች ለዕድገት ፀር ናቸው።
2. ለበጐ አገልግሎት ተግባራት መመሪያ መስጠት የሚገባው መንግሥት ብቻ ነው።
3. መንግሥት የሚያወጣቸው የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት በመንግሥት መ/ቤቶች ብቻ ነው።

***II በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ፡፡***

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ያስ ዕድሜ ጋብቻ፣ | ሀ. ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ። |
| 2. የሀገር ፍቅር መገለጫ፣ | ለ. መልክዓ ምድር። |
| 3. ሙስና፣ | ሐ. ለራስ ወይንም ለሌላው ጥቅም ኢ-ፍትሐዊ ተግባር መፈጸም። |
| 4. ዜግነት፣ | መ. ጐጂ ልማዳዊ ድርጊት። |
| 5. በምክንያት ያልተደገፈ ጭፍን አስተያየት፣ | ሠ. ልዩነት መፍጠር። |
| | ረ. ሕዝብን ማክበር። |
| | ሰ. የአንድ ሀገር ሕጋዊ አባል መሆን። |
| 6. አድልዎ፣ | ሸ. አፍራሽ ተግባር። |

***III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡***

1. ሀገሬን እወዳለሁ ከሚል ዜጋ ከሚጠበቁ ተግባራት መካከል ይጠቀሳል፤
   ሀ. የሕዝቡን ባህልና ቋንቋ ማክበር፣
   ለ. የሥራ ተነሳሽነት መኖር፣
   ሐ. አድሎአዊ ያለመሆን፣
   መ. ሁሉም መልስ ሊሆኑ ይችላሉ።
2. ለሀገራችን ድህነት እንደምክንያት ሊጠቀስ ከሚገባው መካከል አንዱ ነው፤
   ሀ. የተፈጥሮ ሃብት እጦት፣
   ለ. የውሃ እጥረት፣
   ሐ. የሥራ ባህል ያለመዳበር፣
   መ. የርዳታ መቀነስ።
3. የጋራ መገልገያ ንብረቶችን መንከባከብ የሚገባን ለምንድን ነው?
   ሀ. ሕጉ ስለሚያስገድደን፣
   ለ. ጉዳቱ ለእኛም ስለሚተርፍ፣
   ሐ. የሀገር ሀብት እንዳይባክን፣
   መ. ሁሉም መልስ ሊሆን ይችላል።
4. የግዴለሽነት መገለጫ ሊሆን የማይችለው የትኛው ነው?
   ሀ. ቆሻሻን በየቦታው ማዝረክረክ፣
   ለ. መፀዳጃ ቤትን ያለአግባብ መጠቀም፣
   ሐ. የትምህርትን ቤት የጋራ መገልገያዎች በአግባቡ መጠቀም፣
   መ. መልሱ አልተሰጠም።

5. ከሚከተሉት አንዱ በበጐ ፈቃድ የምንሰጠው አገልግሎት ነው።
   ሀ. ስወሳጆችና ስመምህራን በመታዘዝ ግዴታችንን መወጣት፣
   ለ. የትምህርት ሰዓትን በአግባቡ መጠቀም፣
   ሐ. አረጋዊያንና አቅመ ደካሞችን መንከባከብ፣
   መ. ስሀገሪቱ ሕገ መንግሥት ተገዢ መሆን።
6. ሌባንና አድሎአዊ አሠራርን ማጋለጥ፤
   ሀ. ስፖሊስ ብቻ የተተወ ድርሻ ነው፣
   ለ. የፍትሕ አካላትን ብቻ የሚመለከት ነው፣
   ሐ. የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት ነው፣
   መ. ሁሉም መልስ ሊሆኑ ይችላሉ።

## IV የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች ትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::

1. በመወለድ ወይንም በሕግ የሚገኝ መብት______________ ይባላል።
2. ሀገርና ሕዝብን የሚወክል መገለጫ ምልክት____________ ተብሎ ይታወቃል።

## V የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. ከዜጎች ሁሉ ከሚጠበቁ መብትና ግዴታዎች መካከል ሁለቱን ጥቀሱ::
2. ጉጂና አፍራሽ ተግባራት በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የሚያሳድሩትን ተፅእኖ በአጭሩ አብራሩ::